# በራኮ ኦባማ በመመረጡ ዘረኝነት ይጠፋ ይሆን?

የተጻፈ፣ በደስታ ወ/ማሪያም Nov 4, 2008

በባለሞያተኛነትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ የዘንድሮዉን የአሜሪካ 2008 የፕሬዚዳንት ም ርጫ በቅረብ ስከታተለዉ ቆይቻለሁ። ይህም ምርጫ ሕዝብ በሚያስገርምና በሚያስደንቅ ሁኔታ ወጥቶ ለመምረጥ የተንቀሳቀሰበት ስለነበር ካለፉት ምርጫዎች ሁሉ በዓይነቱም ሆነ በመጠኑ የተለየ አድርጎታል። ዘረኝነትና ጾተኝነት የነበረዉ ስርዓት ሁለቱንም የቆዩ ባህሎች ለማ ስወገድ ግድ ባይሆንም ለማዳቀልና ለመበረዝ ጅምሩን የሚያሳይ ነዉ። በተለይም በጥቁር አሜሪካ ታሪክ ዉስጥ አድስ ምዕራፍ ተከፈተ ታሪክ ተሠራ የተባለበት ምርጫ ሆኖአል። ከጥቂት አስርታት ዓመታት በፊት በዛሬትዋ አሜሪካ ሴትና ጥቁር እንኳን ሊመረጡ ቀርተዉ ሊመርጡም አይችሉም ነበር። ሆኖም ዛሬ ሴቶች ፖለቲካዉ መድረቅ ላይ ወጥተዉ የተወዳደሩበት ጥቁር አሜሪካዊ የተመረጠበት ደረጃ ላይ ተደርሶአል። ይህ ዉጤት የተገኘዉ በስርዓቱ ፍላጎትና መልካም ፈቃድ ብቻ ሳይሆን በታሪክ በምናዉቃቸዉ ታጋዮችና ሥማቸዉና ሥራቸዉ ለብዕር ሳይበቃ የቀሩ ክፍሎች ጭምር በከፈሉት መስዋዐትነትና በሠሩት ገድል ነዉ።

ወደ ዋና ቁም ነገር መለስ ልበልና ለመሆኑ በራኮ ባማ በመመረጡ ዘረኝነት ይቆማል ብሎ የሚያስብ ሰው ይኖር ይሆን። 95% በላይ የሚሆነዉ ጥቁር አሜሪካን ከተጠበቀዉ በላይ ስሜት በተሞላበት መንፈስ የመረጠዉ በራኮ ባማን ነበር። በአሜሪካና ትልልቅ ከተማዎች የነበረዉ ደስታና ጭፈራ ከልክ ያለፈ ነበር። በተለይም ሠራተኛዉ ሕዝብ ጥቁር ነጭ ሳይል ያሳየዉ ተሳትፎ "ለዉጥ" እጅግ በጣም ማስፈለጉን የሚያሳይና በስልጣን ላይ ያለዉ አስተዳደር (ወይም ስርዓት) ላይ ሕዝብ ያለዉን ታላቅ ነቀፌታ የሚጠቁም ነበር።

በዚሁ አጋጣሚ የመገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞችና ዜና አቅራቢዎች የሕዝብን ስሜት በደንብ አራግበዉታል። ከዚህም በላይ አንዳንዶቹ ከሞስስ (ኢየሱስ) ጋር ያወዳደሩት አልጠፉም። ታዋቂዉ የፊልም ተዋናኝና ዳሬክተር እስፓኢክ ሊ (Spike Lee) "አዲስ ቀን" "አዲስ ብርሃን" "አዲስ አሜሪካ" "አዲስ ጅማሮ" "ዘረኝነት ያበቃበት ዘመን ነዉ " ሲል በሎስ አንጀለስ ታይምስ ቃሉን ሰጥቷል። በርግጥ በበራኮ ባማ በአሜሪካ ዘረኝነት ይለወጣል ብለን ማለት እንችላለን።

ዘረኝነት ለብዙ ዘመናት ከዚህ ስርዓት ጋር የተሳሰረ፤ ከርየት ዓለሙ ጋር የተጣመረ ፤ ዕለት ከዕለት የዜጎች ግንኙነት ላይ የሚ ከሰት በመሆኑ ዘረኝነት አበቃለት ለማለት ፈጽሞ ያስቸግራል። ዘረኝነት አፍጥጦና አግጦ ባለበት ሁኔታ መሠረታዊ ለዉጥ የሚያመጡ ጥያቄዎች ተነስተዉ በየትኛዉም ቅስቀሳ ላይ ሳይካሄዱና ያለዉ ስርዓት ሳይነካካ፤ ባለበት ሁኔታ እንዴት አድርገን ለዉጥ ማምጣት እንችላለን ብሎ መናገር ይቻላል።

ታዋቂዉ መብት ተሚጋች፤ ማልከም ኤክስ፣ ስለ ስርዓቱ ከዘረኝነት ጋር ያለዉን መንሰኤና ዝምድናዉ ትስስርነታቸዉን ሲያስረዳ "ያለዘረኝነት የካፒታሊስት ስርዓት ፈጽሞ ሊኖር አይችልም " ነው ያለዉ። ታዲያ በዚህ ስርዓት ዉስጥ እየኖርን ዘረኝነት እናጠፋለን ብለን ማስብ አየርና ዉሃ በሌለበት ምድረ በዳ ላይ ዘርቶ እንደማ ብቀል ይሆናል። ይህንን ደግሞ የበራኮ ባማ መመረጥ አያደርገዉም ሊያደርገዉ ም አይችልም። ሊመራዉ የተዘጋጀዉ ስርዓት አይፈቅድለትም። በራኮ ባማ ፤ ጆን መኬይን ያሸነፈዉ በ6% ብልጫ ነዉ። ይህም ማለት ስርዓቱን የሚመሩት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች በራኮ ባማ ጋር ሠላም በመሆናችዉ ምናልባት ስርዓቱን ነፃነታማ ለማስመሰል ካልሆነ በቀር የሚወራዉና በተግባር ያለዉ በፍርድም የማይገናኝ ነዉ። ምናልባትም ኦባማ ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ ስላለዉ በከፊልም ሆን በቃል የገባዉን በተግባር ለመተግበር የተሻለ እድል አለዉ ለማለት ቢቻልም መሠረታዊ ለዉጥ ለማምጣት ግን መሠረታዊ ስርዓትና የአስተሳሰብ ለዉጥ ማድረግ ያስፈልጋል እላለሁ።

በዕውነቱ ለመናገር ከሆነ የስርዓቱ ዘረኝነት አሜሪካንን ወጥሮ ይዞዋታል። በመሆኑም ልክ እንደ ደቡብ አፍሪካ አንድ አራተኛዉ ጥቁር በፍጹም ደህነት ላይ ይገኛል። እንደ አሜሪካ የሕዝብ ቆጠራ ቢሮ መረጃ ጥቁሩ ከነጭ ጋር ሲወዳደር ሁለት እጥፍ ነዉ ፣ በአሁኑ ግዜ ወደ ኮሌጅ ከሚገባዉ ጥቁር ይልቅ ወደ እስር ቤት የሚገባዉ ጥቁር ቁጥር ነው የሚበልጠዉ፡፡ ከ95% በላይ የሚሆነዉ ጥቁር ወጥቶ ቢመርጥም 1.5 ሚሊዮን ያህሉ በተከሰተበት ወንጀል የተነሳ ድምፅ እንዳይሰጥ ታቅቧል። ይህም ስርዓት በዘረጋዉ መሠሪ አካሄድ ሳቢያ አብዛኛዉ ጥቁር ወደ ምርታማነት ከማምራት ይልቅ ወደ ማህበራዊ ዉድቀት የሚያመራ ሁኔታ በመመራታቸዉ ላይ ነዉ። (ሶሰኝነት፤ ሴሴኝነት፤ ወዘተ)

ኦባማ ምነ ዓይነት የስርዓት ለዉጥ ያመጣል ብለን ብንጠይቅ፤ ኦባማ በምርጫ ንግግር ላይ እንደ ትልቅ በሽታ የሚርቀዉ ጉዳይ ዘረኝነት ነበር። ይህ ባይሆን ኖሮ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የዘረኝነት ችግሮች እንደ ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ኦባማ በማንሳት ስለመፍተሄዎቻቸዉ በተወያየ ነበር። አልፎ ተርፎ ስርዓታዊ (institutional) ዘረኝነት በትምህርት ቤት ዉስጥ ተጠይቀዉ ጥቁርነትና ዝቅተኛ ዉጤት በማንነት ላይ ሐፍረትን በሐፍረት ላይ ያስከተሉ ክስተቶች እንደሆኑ አድርጓል።

በራኮ ባማ በምርጫዉ ሲያሸንፍ ባደረገዉ ንግግር ላይ በዕዉነቱ በሪፓብሊካን ፓርቲ መሠረታዊ እሴቶች እንደ በራስ መተማመን፣ የግለሰብ ነፃነት እንደሚያምን በይፋ ገልጾ ነበር። አንደኛዉ ከሁለተኛዉ ጋር የሚጣረስ፣ በራስ ዕድገትና በራስ ወዳድነት ላይ የተመሰረተና፣ ሰፊዉን ሕዝብ ያላማከለ አባባል መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ ነበር።

እራሱን የጥቁር ወግ አጥባቂ ነኝ (conservative) ብሎ ከሚጠራዉ ሸልባይ እስቲል በእስታንፈርድ (Stanford) ዩኒቨርስቲ ደራሴና አምደኛ ስለ ኦባማ በጻፈዉ ጽሁፍ እንዲህ ሲል ይገልጠዋል።

> “There is nothing to support that Obama will lead America into post-racialism. His campaign style revealed a tweaker of the status quo, not a revolutionary, culturally and racially, he is likely to leave America pretty much where he found her.”

ባጭሩ የኦባማ መመረጥ አሜሪካንን ወደ ፀረ-ዘረኝነት ስርዓት ይመራታል የሚል ምንም ዓይነት እምነት የለም። የምርጫዉ ቅስቀሳ የገገርዉን ስርዐት የሚጠብቅና በዚያዉ በዘረኛ መልኩ የሚቀጥል ይመስላል። ከዚህ በላይ በተጠቀሰዉ ትንታኔ እንደ ብዙ ጸሐፊዎች የሚያስገርም ዓይነ ልቦናን (insightful) የሚነካ አባባል ነዉ። ይህንንም በተለይ ለየት የሚያደርገዉ ራሱን ወግ አጥባቂ ነኝ ብሎ ከሚጠራ ምሁር መምጣቱ ተስፋ የተሞላበት አነጋገር አይደለም። በአሜሪካ ሠራተኛ ሕዝብ ጥቁር ነጭ ሳይል መሠረታዊ ለዉጥ ለማምጣት የስርዓቱ መሠረታዊ በሽታዎች በደንብ መነካት ይኖርባቸዋል።

የብዙሃኑ ሠራተኛ ሕዝብ በኦባማ ላይ የጣለዉ ተስፋ ከፍተኛ ቢሆንም ኦባማ የስርዓቱ ደንብ ተከታይ እንደሚሆን ም ንም ጥርጥር እንደሌለቸዉ ብዙዎች ምሁራን አጥብቀዉ ይናገራሉ። ጦርነት እና ዘረኝነት የስርዓቱ መሠረታዊ (essential) ቅመም መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ታሪክን ወደኋላ መለስ ብሎ መመልከት ብቻ ይበቃል። ኦባማ ወዲያዉኑ በተመረጠ ማግስት ስርዓቱን እንዲያስከብርለት አቶ ርሃም አማኑኤልን እንደ ዕልፌኝ አስከልካይ ሲመርጥ፣ ታዲያ የቱ ላይ ነዉ መሠረታዊ ለዉጥ ማምጣት የሚቻለዉ።

የጥቁሮችን አጀንዳ እከታተላለሁ ከሚለዉ ክፍል ከዚህ በታች ያለዉን አስተያየት እንዲህ በሚል ስጥቷል፤

> “I am sorry to burst the bubbles of those of you wept in ecstasy just two days ago but the truth is still the truth, Obama’s Chief of Staff is a pro-war democrat who couldn’t figure out how to beat republicans when the voters turned against them. His appointment is a signal not only that endless war remain on the table, but that choice of Obama over Clinton was a meaningless one. Obama is smarter and savvier than Hillary Clinton and he used those skills to be favored by more big money people than she was. That was why he is the president elect.

ከኦባማ የተፈጠረ ነገር ቢኖር ወጣት ሽማግሌ ጥቁር ነጭ እንዲቀሰቀስ ያደረገዉ “ለዉጥ” (change) የሚለዉ መፈክር እንጅ “ተስፋ” (hope) የሚለዉ አልነበረም። ዉጤት በተሰማ እለት የኤን ፒ አር (NPR) ጋዜጠኛ በመንገድ ላይ ያለዉን የችካጎ ህብረተሰብ በሚጠይቅበት ወቅት፣ “የኦባማ መመረጥ ላንተ ምን ማለት ነዉ ?” ብለዉ ለተጠየቁ ጥ ቄ ሲመልስ፣ ሁሉም ባንድ ድምፅ “ሥራ፤ ሥራ፤ ሥራ . . .” ነበር ያስተጋቡት። ኮርፐሬሽኖችና ባለሀብቶች ለኦባማ ትልቅ ብር ከፍለዉ እንዲመረጥና ያስመረጡት ለሕዝብ ጉዳይና ታችኛዉ የሕብረተሰብ ክፍልን ለመርዳት አይደለም። ይህ ተስፋ ማለትም የሠራተኛዉ ሕዝብ ሥራ ማግኘት በተግባር ካልታዬ ሕዝብ ተስፋ በመቁረጥ ብቻ አስከፉ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ምሁራን አጥብቀዉ አስገንዝበዋል።

የኦባማ ድል ያለጋጠመዉ በጥቁርና በነጮች ሠራተኛ መሃከል ከመራራቅ የልቅ መቀራረብን ቢሆንም፤ ሀቀኛ ቅርበትና ዉህደት ሊመጣ የሚችለዉ ግን ብዙሃኑ ሕዝብ ከጥቂት ሀብታሞች ቁጥጥር ሲላቀቅ ብቻ ነዉ። ጥቂት የጥቁር ሀብታሞች የኦባማን ድል ለመጠቀም እየተሯሯጡ ናቸዉ። እንደ ወል እስትሪት ጆርናል (Wall Street Journal) አባባል፣ “black power brokers ready to rise in tandem with the new president”. እነዚህ የጠገቡ የጥቁርና የነጭ ሀብታሞች ከአሠሪዉ እንጂ ከሠራተኛዉ ሕዝብ ጋር ምንም ዓይነት ገንኙነት እንደሌላቸዉ በተግባር የሚያሳይ ነዉ።

በመጨረሻም ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ጥቁር ወጣት ወደ ፖለቲካዉ ዓለም መምጣትና ነጭ ከጥቁሩ ጋር ተቀላቅሎ ባንድነት መቆማቸዉ እጅግ የሚያስደስት ነዉ። ደጋግሞ እንደታየዉ ዘረኝነት የተቆራኘዉ ከስርዓቱ ጋር በመሆኑ ዘረኝነት ለማጥፋት የሚቻለዉ አይነተኛ የመዋቅር ለዉጥ በማምጣት እንጂ በተግባር ባልተደገፈ ወሬና ተሳትፎ ሊሆን አይችልም።

በሚቀጥለዉ ጽሁፌ የኦባማ ምርጫ ለአፍሪካ አገሮች የሚያመጣዉ ለዉጥ ሊኖር ይችል እንደሆነ በስፋትና በጥልቀት እንመረምራለን።